# ትላንት ነጭ ልብስ፥
# ዛሬ የሮማ ካቶሊክ የአምልኮ ጣዖት (ሐውልት)፥
# ነገ ደግሞ.????

ይበቃል ያረጋል

ሐምሌ ፲፮, ፪ሺ፪ ዓ.ም.

ይሄን ጽሑፍ ለማጻፍ ያነሳሳኝ፥ ሰሞኑን በተለያዩ የሕዝብ መወያያ ድሕረ ገጾችና በራዲዮ ዝግጅቶች ላይ፡ በአዲስ አበባ ቦሌ ደብረ ሠላም መድኃኔዓለም ቤተ-ክርስቲያን ላይ ሰለተተከለውና በአቡነ ጳውሎሰ ሰለተመረቀው የድንጋይ ምስላቸው፥ የተዋሕዶ አማኝ የሆነው ሕዝብ ያሰማውን የመረረ ቅሬታ በማንበቤና በመስማቴ ነው። በዚሁ አጋጣሚ፥ እኔም ከተመረሩትና ካዘኑት ማካከል አንዱ መሆኔን እየገለጽኩኝ፥ ተቃውሟቹህን ማሰማቱን አታቁሙ በርቱ እላለሁ። ሆኖም ግን ዛሬ እኔ ላካፍላቹህ ያሰብኩት፡ ሰለ ነገ ፈራሹ ግዑዝ የድንጋይ ካብ ኢ-ኦርቶዶክሳዊነት ለማሰረዳት አይደለም። ምክንያቱም፥ እኔ ደካማው ልገልጸው ከምችለው በላይ ብዙዎች በሚጋባ ደጋግመው አብራርተውታልና ድግግሞሽ ሰለሚሆን አልፈዋለሁ።

ይህን ጉዳይ አሰመልከቶ፡ ብዙ የተጻፉትን ጽሑፎች ሳነብ፥ የጸሐፊዎቹንም ቁጥር ብዛት እንዲሁም ሰለ ቤተክርስትያኗ ያላቸውን ተቆረቋሪነት ሰመለከት በአንድ በኩል እጅግ ደስ ሲለኝ፥ በሌላ በኩል ደግሞ፥ ብዙም ባይሆን በጥቂቱ ቅሬታ ተሰምቶኛል። ምክንያቱም፥ የካንሳስ ደብረ ሣሕል መድኃኔ ዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምእመናን፥ ላለፉት ፯ አመታት፥ ኧረ ነገረ ሃይማኖቱ ተካደ፥ ኦርቶዶክሳዊው እምነታችን በሮማ ካቶሊኩ "Immaculate Conception" ኑፋቄ ተተካ እያልን ሌት ተቀን ስንጮህ፥ ብዙዎች እውነቱን እያወቃቹህ፥ ከፍርሐት ይሁን ወይንም ከግዴለሽነት ጩኸታችሁን አላሰማቸሁም። ሆኖም ግን፥ዛሬ ለዚህ፡ ነገ ለሚፈርሰው ግዑዝ ድንጋይ (ሐውልት) ቁጣቹህንና ድምጻቹህን ጊዜ ሳታጠፉ ማሰማታቹህ ጥሩ ቢሆንም፥ ጩኸታቹህ ከሁሉም በፊት ቅድሚያ ተሰጥቶት በልባችን ሰለተቀረጸውና ባፋችንም ዘወትር ልንመሰክርለት ሰለሚገባው ሰለ ነገረ ሃይማኖቱ መካድ መሆኑ ቀርቶ፥ አፈታችን ተገትሮ እንደ ጉድፍ አይናችንን ሰለቆረቆረው ሰለ ግዑዙ የድንጋይ ካብ መሆኑን ስለታዘብኩኝ ብቻ ነው። ይህንንም ሰል ለወቀሳ ሳይሆን፥ የጀመራቸሁትን እንድትገፉበት ለማበረታታትና እግረ መንገዴንም ቅደም ተከተሉን ለመጠቆም ያህል ነው።

የዚህ ግዑዝ ድንጋይ (ሐውልት) መተከል እጅግ ቢያሰቆጣንም፥ በሌላ መልኩ ግን የብዙዎቻችንን አይን የከፈተና በቅድስት ቤተክርስቲያናችን ላይ እየተፈጸሙ ያሉትን አሰከፊ ሁኔታዎች በግልጽ እንድናይ ረድቶናል። ይህንንም ለማለት ያሰቻለኝ፡ በተለያዩ ድሕረ-ገጾችና በራድዮን ዝግጅቶች ላይ የቀረቡት አሰተያየቶች በሙሉ፡ በአንድነት ተሰማምተው የመሰከሩት ነገር ቢኖር፥ የሐውልት መትከልን ኢ-ኦርቶዶክሳዊነትንና በተቃራኒው ደግሞ ሐውልት መትከል የሮማ ካቶሊክ ስርአት መሆኑን መሰክረዋል። ለዚህም ማሰረጃ ተብለው ከተጠቀሱት መካከል ብዙዎች የጠቀሱት ነገር ቢኖር፥ በአለም ላይ ያሉትን ኦርቶዶከሳዊ አብያተ ክርስቲያናትን ሲሆን፥ በተለይም ደግሞ፥ በነገረ ሃይማኖቱ ከኛ ጋር ፈጽሞ አንድ የሆኑትን አኀት አብያተ ክርስቲያናት ማለትም፥(የግብጽን፥ የሶርያን፥ የሕንድንና የአርመንን) ቤተክርስቲያናት ለምስክርነት ጠቅሰዋል።

ይህ የሚያሳየው፥ ጽሑፎቹን የጻፉትና በራድዮ ዝግጅቶች ላይ ምሬታቸውን ያሰሙት የተዋሕዶ ልጆች፥ በኦርቶዶክሱ፥ በተለይም ደግሞ በአኀት አብያተ ክርስቲያናትና በሮማ ካቶሊክ መካከል ያለውን ልዩነቶች በሚገባ ለይተው የተረዱና ያነበቡ መሆናቸውን ነው። ይህ ደግሞ የሚያሰደስትና ሁላችንም የተዋሕዶ ልጆች ከአኀት አብያተ ክርስቲያናት ጋራ ያለንን አንድነትና በተቃራኒው ደገሞ ከሮማ ካቶሊክ ጋር ያለንን ልዩነት ጠንቅቆ እንደነሱ ለማወቅ መጽሐፍትን ማገላበጥ ይኖርብናል። ምክንያቱም፥ ሰው በቅጡ ለይቶ ያማያውቀውን ነገር፥ በይበልጥ ደግሞ ሃይማኖትን ያክል ነገር፥ በተራ ወሬ ወይንም በጥራዝ ነጠቅ እውቀት ከዘራፊና ከከሀዲ ሊጠብቀው ፈጽሞ አይችልምና። ለዚህም ጥሩ ማሰረጃው፥ ከላይ ጠቆም ያደረኩት መላው ኦርቶዶክስና አኀት አብያተ ክርስቲያናት በጥብቅ ያወገዙትን፥"Immaculate Conception" በመባል የሚታወቀው የሮማ

ካቶሊክ እምነት በዚህ ፳ ዓመት ውስጥ ቤተክርስቲያናችን ውስጥ ሰርጎ መግባቱ ነው። እንግዲህ ነገ የሚፈርሰውን የግዑዙን ድንጋይ ኢ-ኦርቶዶክሳዊነት ለማስረዳት አኀት አብያተክርስቲያናት ዋና ማሰረጃ ሆነው ከቀረቡ፥ ታዲያ ለምንድነው እስከ ቅርብ ጊዜ በሕይወት የነበሩት ሊቃውንት አባቶቻችን እነ ክቡር መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ "መድሎተ አሚን በሚለው መጽሐፋቸው ተንትነው ያሰቀመጡትንና፥ እነዚሁ አኀት አብያተ ክርስቲያናት ያወገዙትን፥"Immaculate Conception" ቤተክርስቲያናችንን በዚህ ፳ ዓመት ውስጥ እንደወረረሽኝ ሲወራት እንዳልሰማና እንዳላወቀ በመምሰል ዝም መባሉ?

መቼም የእግዚአብሔርን ጥበብና እቅድ ሰለማንረዳ እሱ በፈቀደው ጊዜ ነገሮች ሲፈጸሙ ስናይ እንደነቃለን። ዛሬ በጣዖት መልክ በተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን ላይ የመጣባት ይህ የግዑዝ ድንጋይ ግንባታ፥ ከብዙዎቹ ካባድ ፈተናዎች መካከል፥ አንደኛው ሲሆን፥ እግረ መንገዱን ግን እሱን ለመቃወም ማሰረጃ ፍለጋ መጻሕፍትን እንድንዳስስና እራሳችንንም እንድንጠይቅ አድርጎናል። ለዚህም፥ እግዚአብሔር ይመሰገን። እንግዲህ፥ በየድሕረ-ጋጾቹና በየራድዮኑ ዝግጅቶች ላይ እሮሯቸውን ያሰሙት ወገኖቻችን የድንጋዩን ካብ ለመቃወም ማሰረጃ ፍለጋ ወደ አኀት አብያተ ክርስቲያናት ሄደው እንዳገኙት፥ እናንተም ይሄን የምታነቡ፥ የተዋሕዶ ልጆች፥ እሰቲ አኀት አብያተ ክርስቲያናት እመቤታችንን አሰመልክቶ ሰለ "ጥንተ አብሶ" የሚያምኑትን ተመልከቱና እናንተም ያገኛችሁትን እውነት በድፍረትና በይፋ ለመመሰከር እግዚአብሔር ይርዳቹህ። ለቅምሻ ያህል እንዲረዳቹህ የግብጽ ኦርቶዶክስ ፓትርያርክ አቡነ ሽኑዳ የጻፉትን፥ የሲርያ ኦርቶዶክስ ፓትርያርክ አቡነ ኢግናቲያስ ዛካ የጻፉትን፥ ዛሬ ፓትርያርክ ከመሆናቸው በፊት እራሳቸው አቡነ ጳውሎሰ የጻፉትንና ታላቁ ሊቅ ክቡር መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ "መድሎተ አሚን" በሚለው መጽሐፋቸው (ገጽ ፲፱-፳) የጻፉትን ተመልከቱ። የኦርቶዶከሰ ተዋሕዶና የሮማ ካቶሊክን ልዩነት በግልጽ ያሳያቹሐል።

## The Holy Virgin Mary in The Church's Faith

- The Church believes that the Holy Spirit has sanctified the depository of The Virgin during the pregnancy with Christ. That was according to what the angel said to her "The Holy Spirit will come upon you, and the power of the Highest will overshadow you; therefore, also, that Holy One who is to be born will be called the Son of God"(Luke1:35). The sanctifying by the Holy Spirit of her depository, makes the One born of her, be conceived without the impurity of the original sin. As for The Virgin herself, her mother conceived, like all people, and so The Virgin said in her hymn: "my spirit has rejoiced in God my Savior" (Luke 1:47). That is why the Church does not agree that The Virgin was conceived without the impurity of the original sin, as our brothers the Catholics beleive.
  **(Source) :The Holy Virgin St. Mary,Author: His Holiness Pope Shenouda III Editor: Orthodox Coptic Clerical College, Cairo Edition: 1999**

## Conception and Birth of Mary

- It is noteworthy to mention that the conception of Mary took place according to the natural law for she was of a man (Joachim) and a woman (Hanna).Mary is the daughter of two barren persons just like Isaac, Samuel and John, the Baptist. She inherited, just like them, and like other people, the original sin of Adam and Eve, which is the sin of all humanity starting with Adam who represented his race when he committed sin so his descendents were charged with sin, which could nt be obliterated from falling humanity except by the incarnation of the second hypothesis of the Holy Trinity. That's why the Apostle Paul says:"Wherefore, as by one man sin entered into the world, and death by

sin; and so death passed on all men, for that all have sinned" (Rom.5: 12), and David said:"Behold, I was shapen in iniquity; and in sin did my mother conceive me" (Ps. 51:5.). Of all those who put on flesh, it was only Jesus Christ who was excepted from the legacy of this sin. "Who took everything we have except sin" and who became the propitiator for the sins of the whole world."Being justified freely by his grace through the redemption that is in Christ Jesus: whom God has set forth to be a propitiation through faith in his blood, to declare his righteousness for the remission of sins that are past, through the forbearance of God". (R.3: 23,24). "Wherefore, as by one man sin entered into the world", so by one man it was obliterated (Rom.5: 12:15). Just like all other people, the Virgin Mary, who was, most probably, born in Nazareth, was not without sin.

**(Source):**
**The Holy Virgin Mary in the Syrian Orthodox Church**
**Written by His Holiness Moran Mor Ignatius Zakka I Iwas**
**http://syrianorthodoxchurch.org/library/essays/the-holy-virgin-mary-in-the-syrian-orthodox-church/**

- Ethiopian Orthodox theology sees the blessed Virgin Mary, Mother of God, on the one hand as honored by God above all other creatures in being chosen as the mother og God, the word incarnate, but on the other hand as a human being, born under the shadow of original sin, whose death and assumption into heaven represent the epitome of God's work of salvation for all of humanity in its most exalted member. (page. viii).

- The Virgin Mary occupies a uniqueplace in the Ethiopian Orthodox Church. Her Intercession is continually sought, as evidenced by the common prayer of supplication: "Our Lady Mary, Mother of God, offer up our prayer that our sins may be forgiven." She pleads for the human race. She is not "Immaculate" in the sense that she was born without sin, but in the sense that was specially prepared by the Holy Ghost.(page 147-148).

- Like all daughters and sons of Adam, the Holy Virgin mary died as a result of Adam's sin. "Mary, sprung from Adam, died on consequence of original sin; Adam died in consequence of sin, and the flesh of the Lord, sprung from Mary, died to destroy sin.(page 302).

- For the Ethiopian orthodox Tewahedo Church the Virgin Mary is the example par excellence of obidience and faithfulness to God. She is two-fold virgin, i.e.,virgin both in body and soul, who though not "immaculate" or free from Original sin. yet was all-holy, pure, and chose to actively participate in the saving work of God, His incarnation.(page 306)

**(Source):**
**FILSATA: The Feast of the Assumption of the Virgin Mary and the Mariological Tradition of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church.**
**By Bishop Paulos Yohannes**
**Princeton, New Jersey May 30, 1988**

*መድሎተ አሚን :*

*አዲስ አበባ ነሐሴ ፩ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ. ም. ፭ኛ. ጥያቄ (ገጽ ፲፱-፳)*

*ስሙን ልዮን የሚሉት አንድ ሮማዊ ተነሥቶ: ወልደ አብ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ሥጋ ማርያምን በለበሰ ጊዜ: ሰይፍ በሰገባው እንዲከተትና እንዲቀመጥ አደረበት እንጂ: አልተዋሐደውም: በ፴ ዘመኑ በዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በራሱ ላይ ሲቀመጥ መለኮቱ ከትስብእቱ ተዋሐደ፣ የጸጋ አምላክ ሆነ: መዋቲ ትስብእትም የማይሞት ኾነ ከ፴ ዘመን በፊት የጸጋ አምላክ ስላልሆነ አምላካዊ ሥራ አልሠራም፤ ከተጠመቀ በኋላ ግን የጸጋ አምላክ ስለሆነ ውኃውን ወይን አደረገ ብዙ የአምላክነት ሥራ ሠራ አለ።*

*እንደዚኸውም በንግድ ምክንያት መጥቶ እስክንድርያዊ መሰሎ በኢትዮጵያ የሚኖር አንድ ሰው ተነሥቶ እንዲህ ሲል ተናገረ። እናንተ ኢትዮጵያዊያን ቃል ሥጋ በለበሰ ጊዜ በማኅፀነ ማርያም መንፈስ ቅዱስን ተቀብሎ የባሕርይ አምላክ ሆነ ትላላቹህ በማኅፀን መንፈስ ቅዱስን ሲቀበል ያየው የለም። ሮማዊያን ግን እስከ ፴ ዘመን በሰብአዊ ግብር ኖሮ ሲጠመቅ መንፈስ ቅዱስ ሰው ኹሉ እያየው በራሱ ላይ ስለተቀመጠበት የጸጋ አምላክ ሆኖ የአምላክነት ሥራ ሠራ ይላሉና ከእስክንድርያ ሃይማኖት የሮማ ሃይማኖት ትሻላለች አለ።*

*<u>መልሰ</u>*

*አባ ጳውሊ ሲመልስ፤ ቅዱስ ገብርኤል ለእመቤታችን ሲያበሥራት መንፈስ ቅዱስ ባንቺ ላይ ይመጣል የአብም ኃይሉ ይጋርድሻል: ካንቺ የሚወለደውም ቅዱስ ነው: የልዑል የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል። ፫ቱም አካላት በማኅፀነ ማርያም እንደ አደሩ ተናገሯል። ማደራቸው: አብ ለ<u>አጽንዖ፥ መንፈስ ቅዱስ ለአንጽሖ፥ ወልድ ለለቢሰ ሥጋ ነው</u> እንጂ ፫ቱ ኹሉ ለለቢሰ ሥጋ ያደሩ አይምስልህ።*

*በዚህ ጊዜ መለኮት ርቀቱን ለቆ ሳይገዝፍ፥ ሳይለወጥ: ትስብእትም ግዘፉን ለቆ: ሳይረቅ፥ ሳይለወጥ እንደ ነፍስና እንደ ሥጋ በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነ። ወልድ ለለቢሰ ሥጋ ማለት: ይህ ነው: አብ ለአጽንዖ ማለትም፤ ሰማይ ምድር የመይወስኑትን ምሉእ፥ ሰፉሕ፥ ረቂቅ መሎኮትን: እመቤታችን በጠባብ ማኅፀን እንድትችለው: አጸናት ማለት ነው: <u>መንፈስ ቅዱስ ለአንጽሖ</u> ማለትም: ትስብእትን ከአዳም መርገም አንጽቶ፥ ቀድሶ ለተዋሕዶተ መለኮት የበቃ አደረገው ማለት ነው። ይህን በማኅፀን በረቂቅ ምሥጢር የሠሩትን አምላካዊ ሥራ: በዮርዳኖስ ወልድ ባጭር ቁመት፥ በጠባብ ደረት ተወስኖ ሲጠመቅ በመታየት አብ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ የሚል ድምጸ በማሰማት: መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ተቀምጦ: አብ ልጄ ይህ ነው ብሎ የመሰከረለት ወልድ ይህ ነው ብሎ በጣት ጠቅሶ እንደ ማሳየት በመመስከሩ ገልጸውታል እንጂ እስከዚያ ድረስ ፴ ዘመን መንፈስ ቅዱስ ተለይቶት ኖሮ በዮርዳኖስ አደረበት ማለት አይደለም አለ። <u>ያ ሮማዊ</u> መ<u>ልስ አጥቶ ዝም አለ።</u>*

*አንባቢ ሆይ!!!! ከላይ ቁልጭ ብሎ፥" መንፈስ ቅዱስ ለአንጽሖ ማለትም: ትስብእትን(የማርያምን ሥጋ) ከአዳም መርገም (ከጥንተ አብሶ) አንጽቶ፥ ቀድሶ <u>ለተዋሕዶተ መለኮት የበቃ አደረገው ማለት ነው። ብለው በ፲፬ ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ ሊቃውንት አባቶቻችን: የሮማ ካቶሊኮችን አመስጥረው</u> የረቱበትን የአደራ ቃል: ማን ነው ዛሬ ሊክደው የሚችለው????። እንግዲህ ወገኖቼ፥ ከዚህ የበለጠ: የሃይማኖት ክህደት ከየት ሊመጣ ነው? ከዚህ የበለጠ በሃይማኖት የከፋ ውደቀት ከቶ የለም። ትላንት* "Immaculate Conception" *፥ ዛሬ፥ ግዑዝ ድንጋይ፥ እያሉ ነገ ደግሞ ቤተክርስቲያናችን ጠቅልለው የሮማዊት ቤተ ክርስቲያን ከማድረጋቸው በፊት፥ አይናችንን ከፍተን እውነቱን ለመያዝና፥ ሃይማኖታችንን ለመጠበቅ ብሎም ለመመሰከር በእውቀት እንነሳ።*

*አመሰግናለሁ።*